# ላንተስ መቅኖ

አብርሃም በየነ
ለፀጋየ ድብተራው መታሰቢያ

በጥላቻ መንደር
መዋደድ መፋቀር
ተከባብሮስ መኖር
ሁሉም በዕኩልነት
ሰላም ይሰፍን ይሆን
እያለ ጦርነት?
ጤናስ ይገኝ ይሆን
እየነገሰ ሞት?
የሰላምን መስፈን
ከጦርነት እቶን
የጤንነትንም ልደት
ከበሽታ ማህፀን
ከማህፀነ-ድንቁርና
ብሂለ-ጥበብን_ዕውቀት
ከፍልስፍና ድህነት
የማንነታችንን ተውፊት
ከዘር በሽታ ልክፍት
ማዕረገ ዕኩልነት
ያለመኖራቸውን ሥርየት
ልታመላክተው
ግንባርህን አሳያቸው
ያልከው ትውልድ
ቅኔ አይገባው
የቃላት ሽርብ ገመድ
ብሂለ-ደብተራ

ስለተ-ብዕሩ ካራ
መሆኑን ማጤን
የማይችል
እንግርግብ አሻሮ
ወይ አይሉት ብስል
የተቃጠለ አርሮ
አንጉል ተማሪ
የውሃ ላይ ኩበት
እንኳን ሊሆን መሪ
ስለ ራሱ ህይዎት
ሲያስቡት አንዳንዴ
አያምሱት ነገር
አላባቱ ስንዴ
ወይ አያነፍሱት
ብሊጣ ነጎዴ
አይበሉት ተገምጦ
የዳቦ ወግ ያጣ
አጉል እርሚጦ
የምጣድ ላይ ቂጣ
ስብዕናውን ሽጦ
የፈረንጂ ውሻ
በቁሙ የጀጃ
ዱር እይመኝ ጥሻ
የድሃ ምድጃ
አጉል ተወዝቶ
ደብዛህ ለርሱ ሲባል
መጥፋቱን እረስቶ
እንደ ፍየል ቅጠል
እያመነዠከ

በድኑን ያስገዛል
ችጋር እያከከ።
ግና ግና
የወላድ ማህፀን
በድባቡ ይኑርና
ሞጣና ቢቸና
እንደገና ኮስትርን
ምድረ-አምቦም
ሎሬት ፀጋየን
የተውኔቱን ጃዊሳ
ቋራም ሌላ ካሳ
አሲምባ ተስፋየን
ደብተራው ፀጋዬን
ወልወል ሌላ አሉላ
ገብርዬን መቅደላ
ምደሩ ባልቻን ወልዶ
ሰሜኑን ከደቡብ
የሚያኖር አዋዶ
ትንቢተ-ቀጠሮ
ይሆናል ለነገ
ቃል በውል ተቋጥሮ
የተደነገገ።
ግን እስከዚያው ድረስ
ጃኖህ እንደ በርኖስ
ከላዩ ተጥሎ
አመፅ ተቀጣጥሎ
ድል አስከሚቀዳጅ
አንተን በዝምታው አፍኖ
ያርበኛ ነቁጡን የፋኖ

ያመፅ ነውጡን ማዕበል

የዚያን ትውልድ ፀዳል

የሃገር ኩራት ትምሳሌት

የቅኔ የድጓ የኔታ

የመብት ዕምቢልታ

የዲሞክራሲ መለከት

የጀግና መራራ ሃሞት

የትግል እሳት አለሎ

ያመፅ ትንታግ ቃጠሎ

የኢትዮጵያ ልጅ ብርቅየ

የት ነው ያለኸው? ፀጋየ?

ይላል አገር ላነተስ መቅኖ

መቆም ተስኖት ጀግኖ!!

ለፀጋየ ድብተራው መታሰቢያ

june 3,2008